**_ዶሮዎች_**

**_ጥያቄ 8:- ህዳር 1/2000 የነበሩት ጠቅላላ የዶሮዎች ብዛት_**

**ህዳር 1/2000 ዓ.ም ባለይዞታው የነበሩት ጠቅላላ የዶሮዎች ብዛት በዝርያ ዓይነት ተጠይቆ በተሠጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::**

**ሀ) _ዕንቁላል የሚጥሉ እናት ዶሮዎች_**

**በጥያቄ 8 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ እንቁላል የሚጥሉ እናት ዶሮዎች (በጥናቱ ቀን ዕንቁላል ባይጥሉም) ብዛት በዝርያ ዓይነት ተጠይቆ ይሞላል::**

**ለ) _ዕንቁላል የማይጥሉ እናት ዶሮዎች_**

**በጥያቄ 8 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ዕንቁላል የማይጥሉ እናት ዶሮዎች ብዛት በዝርያ ዓይነት ተጠይቆ ይሞላል:: ዕንቁላል የማይጥሉ እናት ዶሮዎች ሲባል ዕንቁላል መጣል ያቆሙና ለእናትነት ደርሰው ዕንቁላል ጥለው የማያውቁትን መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል::**

**ሐ) _አውራ ዶሮዎች_**

**በጥያቄ 8 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ አውራ የሆኑ ዶሮዎች ብዛት በዝርያ ዓይነት ተጠይቆ ይሞላል::**

**መ) ለ_አውራነት ያልደረሱ ዶሮዎች_**

**በጥያቄ 8 ከተመዘገቡ ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ለአውራነት ያልደረሱ ዶሮዎች ብዛት በዝርያ ዓይነት ተጠይቆ ይሞላል::**

**ሠ) _ቄብ ዶሮዎች_**

**በጥያቄ 8 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ቄብ ዶሮዎች ብዛት በዝርያ ዓይነት ተጠይቆ ይሞላል::**

**ረ) _ጫጩቶች_**

**በጥያቄ 8 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ የጫጩቶች ብዛት በዝርያ ዓይነት ተጠይቆ ይሞላል::**

**_ማስታወሻ:-_**

**ጥያቄ 8= ሀ+ ለ+ ሐ+ መ+ ሠ+ ረ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::**

II. **ባለፉት 12 ወራት ( ህዳር 2/1999 - ህዳር 1 / 2000)**
**የቤት እንስሳት፣ ወይም ንብ የያዙ ቀፎዎች ነበረዎት ?**

**አዎን = 1**
**አልነበረኝም = 2**

*2. በጥያቄ 12 እና 13 ላይ መረጃው ሲሞላ ማስተዋል የሚገባው ጥያቄ 12 ላይ የተሞላ መረጃ በጥያቄ 13 ከተሞላው ጋር እኩል መሆን አለበለዚያም ማነስ እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል::*

*3. በጥያቄ 14 ባለፉት 12 ወራት አማካይ የእንቁላል መጣያ ወቅት ብዛት ሲሞላ አንዲት ዶሮ በዓመቱ ውስጥ ስንት ጊዜ ( ወቅት) እንቁላል እንደምትጥል ተጠይቆ መሞላት አለበት::*

**<u>ጥያቄ 15:</u>- <u>የቤት እንስሳት በሽታና ሕክምና (ከህዳር 2/1999 - ህዳር 1/2000 ዓ.ም)</u>**

**<u>ዓምድ 1</u> - <u>ተራ ቁጥር</u>**

በዚህ ዓምድ በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የቤት እንስሳት ተራ ቁጥር ተሠጥቷል::

**<u>ዓምደ 2</u> -<u>የቤት እንስሳት ዓይነት</u>**

በዚህ ዓምድ የቤት እንስሳት ዓይነት የዳልጋ ከብቶች፣ በጎች፣ ፍየሎች፣ ፈረሶች፣ አህዮች፣ በቅሎዎች፣ ግመሎችና ዶሮዎች ተዘርዝረዋል::

**<u>ዓምድ 3</u> -<u>በበሽታ የተጠቁ ብዛት</u>**

ባለይዞታው ካሉት የቤት እንሰሳት ውስጥ በበሽታ የተጠቁ ካሉ ብዛታቸው በየዓይነታቸውና በጾታቸው ተጠይቆ ይሞላል::

**<u>ዓምድ 4</u>- <u>ሕክምና የተደረገላቸው ብዛት</u>**

ባለይዞታው በዓምድ 3 በበሽታ የተጠቁ ናቸው ብሎ ካስመዘገባቸው የቤት እንሰሳት ውስጥ ሕክምና የተደረገላቸው ካሉ ብዛታቸው በየዓይነታቸውና በጾታቸው ተጠይቆ ይሞላል::

**<u>ጥያቄ 16</u>:- <u>ባለፉት 12 ወራት የተወለዱ፣ የተገዙ፣ በስጦታ የተገኙ፣የተሸጡ፣ የታረዱና በስጦታ የተሰጡ እንደዚሁም በበሽታና በሌላ ምክንያት የሞቱ የቤት እንስሳት ዓይነትና ብዛት በጾታ</u>**

**<u>ዓምድ 1: ተራ ቁጥር:-</u>** በዚህ ዓምድ በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የቤት እንስሳት ተራ ቁጥር ተሰጥቷል::

**<u>ዓምድ 2:-</u> <u>የቤት እንስሳት ዓይነት</u>**

በዚህ ዓምድ የቤት እንስሳት ዓይነት የዳልጋ ከብቶች ፣ በጎች፣ ፍየሉች፣ ፈረሶች፣ አህዮች፣ በቅሎዎች ግመሎችና ዶሮዎች ተዘርዝረዋል::

**ዓምድ 3:- የተወለዱ ብዛት**

በባለይዞታው ቁጥጥር ሥር ከሚገኙት የቤት እንስሳት ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የተወለዱት ጥጆች፣ ግልገሎች፣ ፈረሶች፣ ውርጭላዎች፣ በቅሎዎች፣ ግመሎችና ዶሮዎች ብዛት በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል::

**ዓምድ 4:- የተገዙ ብዛት**

በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የቤት እንስሳት ባለይዞታው ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በግዥ መልክ ያገኛቸው /በገንዘብ/በዓይነት/ ካሉ በዛታቸው በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል::

**ዓምድ 5:- በስጦታ/በሌለ የተገኙ ብዛት**

በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የቤት እንስሳት ዓይነት ባለይዞታው ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በስጦታ/በሌላ (ከግዢና ስጦታ ውጪ) ያገኛቸው ካሉ ብዛታቸው በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል::

**ዓምድ 6:- የተሸጡ ብዛት**

በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የቤት እንስሳት ዓይነት ባለይዞታው ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የሸጣቸው ካሉ ብዛታቸው በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል::

**ዓምድ 7:- የታረዱ ብዛት**

በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የቤት እንስሳት ዓይነት ባለይዞታው ባለፉት 12 ወራት ውስጥ አርዶ ለምግብነት የተጠቀመባቸው ካሉ ብዛታቸው በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል::

**ዓምድ 8:- በስጦታ/በሌላ የተሰጡ ብዛት**

በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የቤት እንስሳት ዓይነት ባለይዞታው ባለፉት 12 ወራት ለሌላ ግለሰብ በስጦታ መልክ የሰጣቸው የቤት እንስሳት ካሉ ብዛታቸው በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል::

**ዓምድ 9:- በበሽታ የሞቱ ብዛት**

ባለፉት 12 ወራት በበሽታ ተጠቅተው የሞቱ የቤት እንስሳት ብዛት በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል::

**ዓምድ 10:- በሌላ ምክንያት የሞቱ ብዛት**

ባለፉት 12 ከበሽታ ውጪ በሌላ ምክንያት ( በውሻ ተነክሰው፣ ገደል ገብተው ፣ በአውሬ ተበልቶ ፣ ወዘተ) የሞተ የቤት እንስሳት ብዛት በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል::

III. ***ባለፉት 12 ወራት የቤት እንስሳት አስከትበዋል ? ( ከህዳር 2/199 - ህዳር 1/2000 )***

***አዎን ከሆነ ኮድ 1 ተሞልቶ ጥያቄ 17 ይቀጥላል***
***የለም ከሆነ ኮድ 2 ተሞልቶ ወደ ጥያቄ 18 ይታለፍ***

**ጥያቄ 17:- የቤት እንስሳት ክትባት በበሽታ ዓይነት**

**ዓምድ 1:- ተራ ቁጥር**

በዚህ ህምድ በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የቤት እንስሳት ተራ ቁጥር ተሰጥቷል፡፡

**ዓምድ 2:- የቤት እንስሳት ዓይነት**

ለዚህ ዓምድ የቤት እንስሳት ዓይነት የዳልጋ ከብቶች፣ በጎች፣ ፍየሎች፣ ፈረሶች፣ አህዮች፣ በቅሎዎች፣ ግመሎችና ዶሮዎች ተዘርዝረዋል፡፡

**ዓምድ 3:- ክትባት የተደረገላቸው ጠቅላላ ብዛት**

በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የቤት እንስሳት ባለፉት 12 ወራት ክትባት ተደርጐ ከሆነ የተከተቡት ብዛት በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በየዓይነታቸው በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል፡፡

**ዓምድ 4- 8 :- ክትባት በበሽታ ዓይነት**

**ዓምድ 4:- ለአባሰንጋ በሽታ**

በዓምድ 3 ክትባት ከተደረገላቸው የቤት እንስሳት ውስጥ በዚህ ዓምድ ለአባሰንጋ በሽታ የተከተቡት ብዛት በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል፡፡

**ዓምድ 5:- ለአባጎርባ በሽታ**

በዓምድ 3 ክትባት ከተደረገላቸው የቤት እንስሳት ውስጥ በዚህ ዓምድ ለአባጎርባ በሽታ የተከተቡት ብዛት በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል፡፡

**ዓምድ 6:- ለሣንባ በሽታ**

በዓምድ 3 ክትባት ከተደረገላቸው የቤት እንስሳት ውስጥ በዚህ ዓምድ ለሣምባ በሽታ የተከተቡት ብዛት በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል፡፡

**ዓምድ 7:- ለጎሮርሳ በሽታ**

በዓምድ 3 ክትባት ከተደረገላቸው የቤት እንስሳት ውስጥ በዚህ ዓምድ ለጎሮርሳ በሽታ የተከተቡት ብዛት በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል፡፡

**<u>ዓምድ 8</u>:- <u>ለደስታ በሽታ</u>**

በዓምድ 3 ክትባት ከተደረገላቸው የቤት እንስሳት ውስጥ በዚህ ዓምድ ለደስታ በሽታ የተከተቡት ብዛት በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል::

**<u>ዓምድ 9:- ለሌላ በሽታ /ይገለፅ</u>**

በዓምድ 3 ክትባት ከተደረገላቸው የቤት እንስሳት ውስጥ ከዓምድ 4 - 8 ከተገለጹት የበሽታ ዓይነቶች ውጪ ለሆነ በሽታ የተከተቡት ብዛት በጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል::

**<u>ማስታወሻ:-</u>**

1. በዓምድ 9 ክትባት የተደረገለት የበሽታ ዓይነት ካለ የበሽታው ስም በእያንዳንዱ የቤት እንስሳት ትይዩ ባለው ቦታ መፃፍ ያስፈልጋል::

2. ክትባት ሲባል ባለይዞታው በቆጠራው ቦታ ወይም በአካባቢው በወረርሽኝ መልክ ለሚከሠተው በሽታ አስቀድሞ ለመከላከል የሚደረግ ሲሆን ይኸውም ለሣንባ ፣ ለጎሮርሳ፣ ለአባጎርባ ለአባሠንጋና ለደስታ የመሳሰሉቱ በሽታዎች ነው::

3. ክትባት የተደረገላቸው የቤት እንስሳት ህክምና እንደተደረገላቸው ተደርጎ መቆጠር የለባቸውም::

4. በበሽታ የሞቱ ብዛት ሲጠየቅ ወድቆ የተሠበረ፣ ገደል የገባ፣ የታረደ፣ በእባብ የተነደፈ፣ በአውሬ፣ የተበላና በውሻ የተነከሰ በዚህ ስር አይካተትም::

5. ህክምና የተደረገላቸው የቤት እንስሳት ሲቆጠር በዘመናዊ የእንስሳት ህክምና መስጫ ጣቢያ ወይም በዘርፉ በሠለጠነ ባለሙያ የታከሙ መሆን አለበት::

**<u>ጥያቄ 18</u> :- <u>የቤት እንስሳት መኖ አጠቃቀም ( ከህዳር 2/1999 - ህዳር 1/2000 ዓ.ም)</u>**

**<u>ዓምድ 1</u> - <u>ተራ ቁጥር</u>**

በዚህ ዓምድ በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የመኖ ዓይነት ተራ ቁጥር ተሠጥቷል::

**<u>ዓምድ 2-</u> <u>የመኖ ዓይነት</u>**

በዚህ ዓምድ የተለያዩ የመኖ ዓይነቶችና ኮዳቸው ተሰጥተዋል::

**ዓምድ 3- ለቤት እንስሳት መኖ ተጠቅመዋል? (አዎን =1 የለም= 2)**

ባለይዞታው በዓምድ 2 የተጠቀሰውን የመኖ ዓይነት መጠቀም አለመጠቀሙ ተጠይቆ መልሱ አዎን ከሆነ ኮድ «1» የለም ከሆነ ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል::

**ዓምድ 4- አዎን ከሆነ ድርሻ በመቶኛ**

በዓምድ 3 ኮድ «1» ለተሞላለት የእያንዳንዱ መኖ ዓይነት ከጠቅላላው የመኖ አጠቃቀም ምን ያህል ድርሻ እንዳለው በመጠየቅና በመቶኛ በማስላት ይመዘገባል:: በዓምድ 3 ኮድ «1» የተሞላላቸው የመቶኛ ድርሻዎቻቸው ተደምረው 100 መምጣት እንዳለባቸው ማስታወስ ያስፈልጋል::

**ዓምድ 5:- በዓምድ 3 አዎን ከሆነ ምንጩ ከየት ነው ?**

በዓምድ 3 መኖ ተጠቅመዋል ለሚለው አዎን ተብሎ ኮድ «1» ከተሞላ ባለይዞታው የተጠቀመውን መኖ በየዓመቱ ከየት እንዳገኘው ተጠይቆ የሰጠው መልስ ከተሰጡት አማራጮች ጋር በማገናዘብ ተስማሚው ኮድ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

**ጥያቄ 19:- ባለፉት 12 ወራት በእንስሳት ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ታቅፈል ?**

ይህ ጥያቄ ለባለይዞታው ቀርቦ የባለይዞታው መልስ አዎ ታቅፊያለሁ የሚል ከሆነ አዎን የሚለው ተሰምሮበት በኮድ መስጫ ቦታው “ 1 ” ይሞላል አልታቀፍኩም የሚል ከሆነ ደግሞ የለም የሚለው ተሰምሮበት በኮድ መስጫው “ 2 ” ይሞላል::

**ማስታወሻ**

ለጥያቄ 19 ለተዘረዘሩት የተለያዩ የእንስሳት ኤክስቴንሽን ፓኬጆች መጠነኛ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚከተለውን አጭር መግለጫ ይመልከቱ:-

1. **የወተት ሃብት ልማት ኤክስቴንሽን ፓኬጅ**

ፓኬጁ አርሶ አደሩ ከአንድ ላም ያገኝ የነበረውን ዝቅተኛ የወተት ምርት ለማሻሻል ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን በውስጡም የሚከተሉትን ያጠቃልላል::

ሀ. የክልስ ክበድ ጊደር ስርጭት
ለ. የሰው ሰራሽ ማዳቀል አገልግሎት
ሐ. የኮርማ አገልግሎት ናቸው::

ከዚህ ጋር ተያይዞም ከሀ-ሐ ከተገለጹት አማራጮች ጋር የተሻሻሉ የእንስሳት መኖ ስርጭት/አጠቃቀም፣ የእንስሳት ጤና እንክብካቤ (ከበሽታዎችና ከጥገኛ ትሎች) የመጠለያ ዝግጅት፣ የጥጃ እንክብካቤ ወዘተ. . . በጣምራ መካሄድ ይኖርባቸዋል::

## 2. <u>የሥጋ ምርት ማሻሻያ ፓኬጅ</u>

ፓኬጁ ገበሬው ያሉትን (ያረባቸውንም ሆነ በግዢ ያመጣቸውን) እንስሳት ለእርሻና ለእርባታ ከማዋል በተጨማሪ እንስሳቱን ለሥጋ ምርት ለመጠቀም እንዲያስችለው ታስቦ የተዘጋጀ ነው:: በመሆኑም በዚህ ፓኬጅ ሥር የሚጠቃለሉት የሚከተሉት ይሆናሉ::

ሀ. የዳልጋ ከብት ማድለብ ፓኬጅ

ለ. የበግና ፍየል ማድለብ ፓኬጅ ሲሆኑ

ከእነዚህም ጋር የተሻሻለ የእንስሳት መኖ መጠቀም ፣ የእንስሳት ጤና እንክብካቤ ወዘተ. . . በጣምራ ይካሄዳሉ::

## 3. <u>የዶሮ ምርት ማሻሻያ ፓኬጅ</u>

በገበሬው ዘንድ እየተከናወነ ያለው የዶሮ አረባብ ኋላ ቀር በመሆኑ ከዘርፉ የሚገኘው የእንቁላል ምርትም ሆነ ሥጋ በጣም አናሳ ነው:: ስለሆነም ይህን ለማሻሻል ፓኬጁ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል:: በዚህ ፓኬጅ የሚካተቱት:-

ሀ/ ጥምር ፓኬጅ :- የተሻሻለ አንድ አውራና የሦስት ወር ቄብ ዶሮዎችን ለገበሬው በመስጠት ማርባትና የእንቁላል ምርት ማሻሻል ነው::

ለ/ ነጠላ ፓኬጅ :- አንድ የተሻሻለ አውራ ዶሮን ለገበሬ በመስጠት ከሀገር ውስጥ እንቁላል ጣይ ዶሮ ጋር እነዲገናኝ በማድረግ የእንቁላል ምርትን ማሻሻል ነው::

ሐ/ የአበሻ ዶሮ ማሻሻያ ፓኬጅ

መ/ የአንድ ቀን ጫጩት ፓከጅ* ናቸው::

ከላይ ከተዘረዘሩት ጋር በጣምራ የተሻሻለ የዶሮ መኖ አጠቃቀም የጤና እንክብካቤ ወዘተ. መከናወን ይኖርባቸዋል::

**4.** <u>**የማርና የሰም ልማት ፓኬጅ**</u> :- ፓኬጁ ገበሬው ከባሕላዊ ፣ከሽግግር፣ ወይም ከዘመናዊ ቀፎ የሚያገኘውን የማርም ሆነ የሰም ምርት ከፍ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው::

### <u>ጥያቄ 20:</u>- <u>ከታቀፉ በየትኛው የእንስሳት ኤክስቴንሽን ፓኬጅ</u>

በጥያቄ 19፣ ባለይዞታው ታቅፌያለሁ ብሎ ኮድ "1" ከተሞላለት የታቀፈበት ፓኬጅ ዓይነት ተጠይቆ ከተሰጡት አማራጮች በመምረጥ ኮዱ በተሰጠው ቦታ ይሞላል::

** የአንድ ቀን ጫጩት ፓኬጅ: እንደተፈለፈሉ (ከእንኩቤተር እንደወጡ) በገበሬ ደረጃ ከተሠራ ማሞቂያ ጋር ለገበሬዎች በመስጠት አሳድገው እንዲጠቀሙ ማድረግ ነው::*